የሰ/መ/ቁ. 34504

ሚያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ አበባው የሺድንበር አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሣ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ የመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት መስከረም 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 14/95 በሆነው በ10/7/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ትዕዛዝ ስላልተነሳ በመዝገቡ ላይ ክርክር መቀጠል አልተቻለም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 16552 በሆነው ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ብይኑን አጽንቶታል፡፡ እንደገና በይግባኝ የመረመረው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በሆነው መዝገብ ኀዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መልስ ሰጭ የሆነውን የአሁኑን አመልካችን ሳይጠራውና ሳያከራክር "ምንም እንኳን ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም" በማለት ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተሠጠ ውሣኔ የሌለ በመሆኑ የመጀመሪያው ክስ ቢዘጋለትም እንደ ገና እንዲንቀሳቀስለት በተወሰነው መሠረት ክርክሩ እንዲቀጥል የተፈጠረው ስህተት ተስተካክሏል በማለት ውሣኔውን በመለወጡ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ ለተጠሪ ደርሶት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ በአጭሩ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ቤቶች የተከራካሪ ወገኖች ማንኛቸውም አቤቱታና ቅሬታ በዳኝነት ሊታይ የሚችለው በሕግ በተመለከቱ ሥርዓቶች ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምንም እንኳን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተፈጠረውን ስህተት ለማረም የአሁኑን አመልካች ሳይጠራውና ሳያከራክረው የአንደኛውን ወገን ቅሬታና ክርክር ብቻ በመስማት ውሣኔ ላይ መድረሱ የአንደኛውን ወገን የመሰማት መበት የተጋፋና ከሥነ - ሥርዓት ሕግ ውጪ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ ሥር በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ያልሠረዘ እንደሆነ ይግባኙ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ መልስ ሰጭው ቀርቦ እንዲከራከር መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህን በሕግ የተመለከተውን የመሰማት ሕገ-መንግሥታዊ መብት /the right to be heard/ ባልጠበቀ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በየትኛውም መመዘኛ ፍትሐዊና የሕግ መሠረት አለው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ አንደኛውን ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በ13/3/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ግልባጭ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ